
በክርስቲያናዊ አስተምህሮ አገልግሎት

# የዮሐንስ ወንጌል

በክርስቲያናዊ አስተምህሮ አገልግሎት

**እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።**



2023

በክርስቲያናዊ አስተምህሮ አገልግሎት

## ማውጫ


1. መግቢያ ... 3
2. መሠረታዊ እውነታ ፈላጊ ጥያቄዎች ... 4
3. የመሲሁ ማንነት 1፡1-18 ... 6
4. የመሲሁ አገልግሎት የአይሁዶችን ልብ በቀላሉ የሳበበት ጊዜ 1፡19-4፡54 ... 8
5. የመሲሁን አገልግሎት አይሁዶች በጥርጣሬ በማየታቸው ምክንያት አለመግባባት መብቀል የጀመረበት ጊዜ 5፡1-6፡71 ... 12
6. በመሲሁ አገልግሎት አይሁዶች ባለማመናቸው ምክንያት የክርክር እና የጭቅጭቅ ጊዜ 7፡1-10፡39 ... 15
7. የመሲሁ አገልገሎት በአይሁዶች መካከል የፈጠርው ጭቅጭቅ ወደ ግድያ መፈለግ ያደገበት ጊዜ 10፡40 -12፡36 ... 18
8. መሲሁ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብቻ ያደረገው ልዩ የስብሰባ ጊዜ እና ጸሎቱ 13፡1-17፡26 ...19
9. የመሲሁ መገደል እና ትንሳዔው 18፡1-20፡31 ...20

# 1 . መግቢያ

- ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሐሳብ ጋር ያለው ግንኙነት
  - በናዝሬት ከተማ ያደገው ኢየሱስ አስቀድሞ በሕግ ፣በነቢያት እና በመዝሙራት ሲነገርለት የነበረው፤
  - ሲጠበቅ የነበረው መሲህ እርሱ ኢየሱስ እንደ ሆነ ለእስራኤላዊያን ለማሳሰብ እንደ ድልድል የሚያገለግል፤
  - ክርስቶስን ለማሳወቅ እንጂ አይሁዳዊነትን ለመተካት የመጣ አዲስ ትምህርት አለመሆኑን ለአይሁድ ሕዝብ ለማሳሰብ የሚረዳ መጽሐፍ ነው፤
  - በመጽሐፉም የተደረጉት ታዓምራቶች ሁሉ ይህንን የሚያመለክቱ "ምልክቶች" ናቸው። ለምሳሌ፡-
    - በቃና ገሊላ የመጀመሪያው ምልክት ብሎ ይጀምራል ጸሀፊው።
    - የሳምራዊቷ ሴት ንግግር በራሱ ይህንን አመላካች ነው። 4፡25
    - ወደ ዮሐንስ መጥመቁ የተላኩት መልዕክተኞች።1፡19-21
- ከሌሎቹ ከሶስቱ ወንጌላት ጋር ያለው ግንኙነት
  - የተመሳሳይነት ችግር ከሥነ-ጹሑፋዊ እይታ አንጻር ከሚታይባቸው ከተቀሩት ወንጌላት የተመሳሳይነት ችግር የማይታይበት መጽሐፍ ሲሆን
  - በአቀራረቡም ሆነ በስነ-ጹሑፋዊ ይዘቱ ከሌሎቹ ወንጌላት ይለያል
  - በይዘቱ ልዩነት ይታይበት እንጂ እንደ ሌሎቹ ወንጌላት የዮሐንስም ወንጌላት ስለ ኢየሱስ መሲህነትና ትክክኛነት አብሳሪ መጽሐፍ ነው።
- ስለ ወንጌሉ አጠቃላይ መግለጫ
  - በይዘቱ ሥነ-መለኮታዊ ነው። ማለትም ስለ ክርስቶስ፣ስለ እግዚአብሔር አብ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፣ ስለ መዳን ሁሉ መሰረታዊ አስተምህሮዎችን ያዘለ ነው።
  - በትረካው መሲሁ ከብዙሐን ሕዝብ ጋር ካደረጋቸው ግንኙነቶች ይልቅ ከግለሰቦች ጋር በተናጠል ያደረጋቸውን ግንኙነቶች ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶበታል።

- በሌሎች ወንጌላት ከተጠቀሱት ተዓምራቶች መካከል ሁለቱ ብቻ የተጠቀሱ ሲሆን ( 5ሺህ ሕዝብ መመገቡ፣ በውሃ ላይ መራመዱ) የተቀሩት አምስቱ ተዓምራቶች በዚህ ወንጌል ብቻ የሚገኙ ናቸው።
- በትምህርቱ ከሥነ- ምግባር ይልቅ በክርስቶስ ማንነት ላይ አጽንኦት ይሰጣል።

  ለምሳሌ፡-

- እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ 6፡35
- እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ 8፡12 ፣ 9፡5
- እኔ የበጎች በር ነኝ 10፡7
- መልካም እረኛ እኔ ነኝ 10፡11፣14
- ትንሣኤ እና ሕይወት እኔ ነኝ 11፡25
- እኔ መንገድ እውነት እና ሕይወት ነኝ 14፡6
- እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ 15፡1

# 2. መሠረታዊ እውነታ ፈላጊ ጥያቄዎች

አንድን መጽሐፍ ለማጥናት ስንነሳ ዘወትር ልንከተለው የሚገባ የአጠናን መንገድ የመጽሐፉን ታሪካዊ ዳራ ፣ የመጽሐፉን መልክ ፣ ሥነ-ጹሑፋዊ ውቅሩን በውል ማጤን ነው ። በዚህ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከግንዛቤ በማስገባት የዮሐንስን ወንጌል ለማጥናት እንሞክራለን።

1. የመጽሐፉ ደራሲ/ጸሐፊ
   - የዚህ ጽሑፍ ባለቤት ተደርጎ የሚታየው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው።
   - የዘብዲዮስ እና የሰሎሜ ልጅ ፣ የያዕቆብ ወንድም በዓሳ አጥማጅነት የሚተዳደሩ ነበር።
   - አጠራሩ ከዓሳ አጥማጅነት ሥራው ላይ ነው የተጠራው።
   - አስቀድሞም የመጥመቁ ዮሐንስ ደቀመዝሙር ነበር።
   - ከስምዖን ወንድም ከእንድርያስ ጋር ነበር በወቅቱ።1፡35-41
   - ባሕሪው ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር በስተጀመሪያው ላይ ያለመረጋጋት የሚታይበት ከዚህም የተነሳ የነጎድጓድ ልጆች ተብለው እስኪጠሩ ደርሰው ነበር፤
   - ጸሎታቸው ልመናቸው ሥልጣንን የበላይነትን መሰረት ያደረገ ነበር፤
   - በኋላ ላይ ግን የፍቅር ሰው ወደ መባል የመጣ ነው፡፤
   - ከወንጌሉ አንጻር ሲታይ ስለ አይሁድ ወገኖች ታሪክ ባህል በዓላት እንዲሁም አካባቢዎች ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ይመስላል። ምክንያቱም በጹሑፉቹ ውስጥ እነዚህ ጉዳዮች በግልጽ ይታያሉ። 11፡18፤18፡1፤9፡7

- ኢየሱስ ለፍርድ ወደ ሊቀካናቱ ግቢ ሲወሰድ ከሊቀ ካህናቱ ጋር ትውውቅ ስለ ነበረው የሚተላለፈውን ፍርድ ለመከታተል እድል ነበረው። 18፡15-16 እንዲሁም በመጨረሻው እራት በፈተናውና በመስቀሉ ስርም ኢየሱስ አጠገብ እንደ ነበር የሚያመለከቱ ነገሮች በወንጌሉ ተጠቅሰዋል።13፡23፤19፡26-27
- ጌታ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ውይይት እርሱ ቤት ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል።
- ከሐዋርያቱ ሁሉ ረጅም ጊዜ እንደ ነበረው እና በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ማብቃያ ላይ እንደ ሞትም ይገመታል።
- ከዚህ ወንጌል በተጨማሪም 3ቱን መልዕክቶች እና የራዕይን መልዕክት እርሱ እንደ ጻፈ ይገመታል።
  - ✓ ወንጌሉ በይዘቱ ልዩ እንደ ሆነ ሁሉ 3ቱም መልዕክቶች በይዘታቸው ከሌሎች መልዕክቶች ይለያሉ
  - ✓የመጨረሻው መጽሐፍም በይዘቱ በአቀራረቡ ሁሉ እጅግ የተለየ መጽሀፍ ነው።

2. የመጽሐፉ ተቀባዮች
   - በምዕራፍ 20፡31 ላይ እንደ ተገለጸው መሰረት በኢየሱስ መሲህነት እና የእግዚአብሔ ልጅ መሆንን ለማያምኑ ሁሉ የተጻፈ ይመስላል ከአቀራረቡ፤
   - በተለይም ደግሞ አይሁዶችን መሰረት ያደረገ ይመስላል።
3. የመጽሐፉ መቸት
   - ብዙዎች የሚስማሙበት ኢየሩሳሌም በ70ዓ.ም ከፈረሰች በኋላ ከ80-90ዓ.ም እንደሆነ ይገመታል።
   - ሐዋርያው ከኤፌሶን ከተማ ሆኖ እንደ ጻፈውም በብዙዎች ዘንዳ ታማኝነት አለው።
4. የመጽሐፉ መሰረታዊ ዓላማ
   - በምዕ20፡31 መሰረት ሰዎች ኢየሱስ እርሱ መሲሁ እና የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በማመን የዘላለም ሕይወት እንዲያገኙ ለመርዳት ነው።
5. የተጻፈበት ዋና ምክንያት
   - እምነትን አጥብቆ ስለመያዝ / Apologetic / የማስተማር ነው
   - ወንጌሉን በሚሰሙት እና በሚያነቡት ልብ ውስጥ እምነትን ለመፍጠር
   - ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ሥራ በሚገባ ለማስገንዘብ ነው።
6. የመጽሐፉ ልዩ ባህሪ
   - ከሌሎች መጻሕፍት በተሻለ መልኩ ስለ ክርስቶስ ማንነት ቀጥተኛ አስተምህሮ መያዙ፤
   - በ7 ታዓምራት ላይ ብቻ ተመስርቶ የመሲሁን ማንነት ገላጭ መሆኑ፤
   - በሌሎች ወንጌላት ውስጥ ሽፋን ያልተሠጠባቸው ትምህርቶች እና ታዓምራቶች መካተታቸው፤
     - ✓የወንጌሉ መግቢያ ሀሳብ

✓የቃና ገሊላው ታዓምር

✓የሰማራዊቷ ሴት ታሪክ

✓የአመንዝራዊቷ ሴት ታሪክ

✓ክርስቶስን ወደ ሞት ያደረሰው የአልዓዛር ሞት እና ትንሳኤው

✓በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተዘገቡት የጌታ ትምህርቶች እንደ ሌሎቹ ወንጌላት በቀጥታ ሳይሆን ፣ ሰዎች ተዓምራቱን ወይም ያደረገውን ምልክት አይተው ወደ እርሱ ሲመጡ ያስተማራቸው ትምህርቶች ናቸው።

- ወንጌሉ መሲሁ ከግለሰቦች ጋር ያደረገውን ውይይት ከሌሎች ወንጌሎች በተሻለ መያዙ ምሳሌ፡-

✓የአሁድ ምኩራብ አለቃ ፊሳዊው ኒቆዲሞስ

✓ሳምራዊቷ ሴት

✓ማሪያም እና ማርታ እንዲሁም በወንማቸው በአልዛር ቤት ያለው የጠበቀ ወዳጅነት

✓ከናትናኤል ጋር የነበረው ቃለ ምልልስ

7. አስተዋፅዖ

- የመሲሁ ማንነት 1፡1-18
- የመሲሁ አገልግሎት የአይሁዶችን ቀልብ በቀላሉ የሳበበት ጊዜ 1፡19-4፡54
- የመሲሁን አገልግሎት አይሁዶች በጥርጣሬ በማየታቸው ምክንያት አለመግባባት መብቀል የጀመረበት ጊዜ 5፡1-6፡71
- በመሲሁ አገልግሎት አይሁዶች ባለማመናቸው ምክንያት የክርክር እና የጭቅጭቅ ጊዜ 7፡1-10፡39
- የመሲሁ አገልገሎት በአይሁዶች መካከል የፈጠር ጭቅጭቅ ወደ ግድያ መፈለግ ያደገበት ጊዜ 10፡40 - 12፡36
- መሲሁ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብቻ ያደረገው ልዩ የስብሰባ ጊዜ እና ጸሎቱ 13፡1-17፡26
- የመሲሁ መገደል እና ትንሳዔው 18፡1-20፡31

# 3. የመሲሁ ማንነት 1፡1-18

ይህ የምንባብ ክፍል የአጠቃላዩ የዩሐንስ ወንጌል መጽሐፍ መግቢያ ተደርጎም ይወሰዳል። በአርግጥም በዚህች አጭር በምትመስል የምንባብ ክፍል ውስጥ ከዚህ በፊት አይተነው በማናውቀው መንገድ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት የምናይበት ክፍል ነው። ዘርዘር አድርጎ ማየት ቢቻልም እንኳ ነገር ግን በዚህ ኮርስ ልናስተውል የሚገባው ነጥብ እንደዚህ ተቀምጦአል።

1. ክርስቶስ "ቃል" ተብሎ መገለጹ

*"በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።"*

- የቃሉ አገባብ በዚህ ስፍራ በግሪኩ ሎጎስ ተብሎ የሚታወቀው የግሪክ ቃል ነው። በመሆኑም ግሪኮች ይህን ቃል ሰብዕና ወይም እኔነት ላለው ነገር አይጠቀሙትም በመሆኑም ይህንን ግዙፍ ዓለም የሚመራ መርህ አድርገው ያስቡታል። አይሁድ ግን በተቃራኒው ይጠቀሙታል። በእኛ አውድ ግን ይህ ሎጎስ ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ዐ.ነገር እንደሆነም አድርገው የሚመለከቱ የእምነት ተቋማት አሉ። ነገር ግን "ቃል" ወይም "ሎጎስ" በዚህ የምንባብ ክፍል አውድ መሰረት

*ሀ. የራሱ እኔነት ያለው ነው* - `Logos` የሚለው ቃል አይሁድ የራሱ ስሜት ፈቃድ እና እውቀት ላለው ነገር መገለጫ አድርገው ይጠቀሙታል። በመሆኑም ዮሐንስ ክርስቶስን በቅድመ አለመ የነበረበትን ሁኔታ ለመግለፅ ተጠቅሞበታል።

*ለ. መለኮትነት ያለው ነው*- መለኮት የሚልው ሀሳብ አምላክን አምላክ ሊያስብሉ የሚችሉ ጉዳዮችን ያዘለ ነው። አንድ ነገር መለኮት ለመባል ዘላለማዊ፣ ሁሉን ቻይ ፣ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ እና ሁሉ ነገር አዋቂ መሆን ይጠበቅበታል። መለኮት የሆነ ነገር ሁሉ ደግሞ አምላክ መባል ገንዘቡ ነው።በመሆኑም በዮሐንስ አገላለጽ ቃል እግዚአብሔር ነበር ይለናል ይህም ቃልም አምላክ ነበር በማለት።

*ሐ. ከእግዚአብሔር ጋር የነበር* - ይህ አገላለጽ ስለ በእግዚአብሔር ሶስትነት ውስጥ ያለውን ህብረት አስገንዛቢ ክፍል ነው። ከቅደመ ዓለም ጀምሮ አብሮ የነበረ እንጂ ከጊዜ በኋላ አብሮነትን ያገኘ አይልም።በመሆኑም ቃል (ክርስቶስ) ከመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ ደገሞም እርሱ ራሱ እግዚአብሔር የነበረ ነው ይለናል። በዮሐንስ አገላለጽ ቃል እግዚአብሔር ወይም አምላክ በመሆኑ ሁሉ ነገር እንኳን ሲፈጠር በእርሱ በኩል የተፈጠረ እና ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም ነገር እንዳልነበር በግልጽ ያስረዳል። በእርግጥ የሁሉ ነገር ፈጣሪ እንጂ ቅድሚያ ተፈጣሪ ስለ መሆኑ የሚገልጽ አንዳችም ሃሳብ የለም። አይሁድም ይህንን ሀሳብ ሊገነዘቡት ባለመቻላቸው መለኮታዊ ማንነቱን ለመናገር በሚፈልግ ጊዜ ሁሉ አለመግባባቶች ይፈጠሩ ነበር። አብርሃም "ሳይወለድ እኔ አለሁ፣ ከሰማይ እኔ ወርድሁ፣ ከአባቴ ዘንድ ወጥቼ መጣሁ ፣ አባቱ እቅፍ የነበረው ፣ እኔ አውቀዋለሁ አይቼዋለሁ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ ሁሉ አይሁድ ይጣሉት ነበር።

2. ክርስቶስ የሰዎች ሁሉ ሕይወት መሆኑ - *"በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች"*

- ይህንን ሀሳብ በሁለት ገጽ መመልከቱ ተገቢ ነው

ሀ. ክርስቶስ ለሰዎች የዘላለም ሕይወት ነው። ኤፌ2፡1-10 እርሱ ከሞት በተነሳ ጊዜ እኛም ከእርሱ ጋር ሕይወትን አገኘን። በመሆኑም ለክርስቶስ የተሰጠው ሕይወት በእምነት ተካፋዮች ሆነናል።

ለ. ክርስቶስ ለትክክለኛ የሕይወት አኗኗር ምሳሌ ነው። ዮሐ3፡19-21 ክፉ ማድረግ እንደ ጨለማ ሲመሰል እውነት እና በጎ ማድረግ ደግሞ እንደ ብርሃን ተመስሎአል። በመሆኑም በእርግጥም እግዚአብሔርን አይቻለው የሚል ሰው ሁሉ ክርስቶስ እንደ ተመላለሰ በብርሃን ይመላለሳል።

3. ክርስቶስ ከዚህች ዓለም ጋር የነበረው ግንኙነት - *"ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር።በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም።የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም።"*

- ይህ የሰዎች ልጆች ብርሃን የሆነው ቃል ወደ ዚህች ዓለም ይመጣ ነበር። በእውነትም እንደ ዮሐንስ አባባል ቃል በስጋ ከመምጣቱ በፊት ወደዚህች ዓለም ይመጣ ነበር።አሁን ግን ሰው ሆኖ በመካከላችን ተገኘ የገዛ ወገኖቹ የሆኑት አይሁድ በማንነቱ አልተቀበሉትም አላወቁትምና።
- ነገር ግን የእርሱን ማንነት በውል ተረድተው ማለትም ኢየሱስ እርሱ መሲህ እና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የተረዱ እና በዚህ መልክ ያመኑት ልዩ የሆነ እድል ተሰጣቸው እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ስልጣን። ማንም በራሱ ሥራ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ብቃት ያለው የለም ! ደግሞም የእግዚአብሔር ልጅ አንድ እርሱ ብቻ ነው። ይህም ሥልጣን መንፈሳዊ ክብርን ውልደትን እና እንደ ተስፋው ቃል የተስፋው ዘር መሆንን ያስገኛል።

4. ክርስቶስ ሰው መሆኑ - *"ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።"*

- የቃል ሥጋ የመሆን ምሥጢር ታላቅ ነው። አምላክ ሰው ሆነ ብለን አሜን ከማለት በቀር ስለ አካኋኑ ምንም ዓይነት ገለጻ መስጠት ያስቸግራል። መጽሐፉም ለምን ሰው መሆን እንዳስፈለገው እንጂ እንዴት ሰው እንደ ሆነ ብዙም ማብራሪያ አልሰጠም።
- በመሆኑም ክርስቶስ በሁለት ተፈጥሮ በአንድ ማንነት ይዞ የሚኖር ነው። ለአብ የተስተካከለ ክብር እንጂ ሰው በመሆኑ ምክንያት መለኮትነቱ ላይ የመጣ ለውጥ የለም። መለኮታዊ የሆነው ቃል ሰብዓዊ ኢየሱስ ሆነ። በእርግጥ መጽሐፉ ከእናቱ ማህጸን ወይም ከሰው ከመሆነው ነገር መውሰዱንም ሆነ አለመውሰዱን ምንም ዓይነት ማረጋገጫ አይሰጥም።

- ጸጋን እና እውነትን ተሞልቶ በሰዎች መካከል ሆነ ተገለጠ፤ በእኛ አደረ ሲል ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳኑ የመቅድስ ስራ የተወሰደ ሃሳብ ሲሆን "በመካከላችሁ አድር ዘንድ መቅደስን ስሩልኝ" ብሎ ለሙሴ እንዳዘዘው ሁሉ ደግሞም ክብሩ በመቅደሱ ይታይ እንደነበር አመላካች ሐሳብ ነው።
- ዛሬም በአዲሱ ኪዳን ክርስቶስ ኢየሱስ ለሰዎች ልጆች እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ጸጋ እና እውነትን ተሞልቶ መጣ። በመሆኑም በጸጋ ላይ ጸጋ ሲል በአንድ በረከት ላይ ሌላ በረከትን ተቀበልን ማለቱ ሲሆን ኢየሱስም የተትረፈረፈ ሕይወት እንዲሆንልን እንደ መጣ እርሱም መስክሮአል። (10:10)
- ክብሩን ገለጠ ክብሩንም በእርግጥ አየን ስለዚህም መሲሁ እርሱ መሆኑን ተቀበልን አመንን። (1:14; 2፡11; 11:4, 11:40, 12:41,)

# 4. የመሢሁ አገልግሎት የአይሁዶችን ልብ በቀላሉ የሳበበት ጊዜ 1፡19- 4:54

በዚህ መጽሐፍ ዘጋቢ መሰረት የናዝሬቱን ኢየሱስን "መሲሁ" ስለ መሆኑ ያለ ብዙ ክርክር እና ጥርጥር ከተቀበሉት መካከል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው። በመሆኑም በዚህ ልብ እና መንፈስ ረጋ ብሎ ማጤን ተገቢ ነው።

4.1. የመጥመቁ ዮሐንስ ምስክርነት (በዮርዳኖስ ማዶ በቢታኒያ በቤተ ራባ) 1፡19-34፤ 1፡15


- መጥመቁ ዮሐንስ እና የናዝሬቱ ኢየሱስ በአካል እንደ ሰው አይተዋወቁም ነገር ግን ከዮሐንስ መጥመቁ ምስክርነት እንደ ምንረዳው በውሃ እንዲያጠምቅ እግዚአብሔር የላከው በቅድሚያ መሲሁ ለሕዝብ እንዲገለጥ እና መንፈስ ቅዱስ ሲወርድበት የምታየው እርሱ መሲሁ ነው ብሎት እንደነበር መስክርአል።
- በመሆኑም ሰዎች ስለ እርሱ ማንነት ሲጠይቁ የመለሰው መልስ እርሱ መሲሁ ሳይሆን በኢሳያስ ትንቢት የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ ይጮሃል የተባለለት ያ ሰው ነኝ እኔ ብሎአል።
- ነገር ግን ስለ መሲሁ የእግዚአብሔር በግ ስለመሆኑ ፣ ከእርሱ ይልቅ የከመበረ ስለመሆኑ፣ በመንፈስ ቅዱስ አጥማቂ ስለመሆኑ ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ ስለመሆኑ ለሕዝብ መስከረ።

4.2. የደቀመዛሙርት መጠራት እና መሲሁን መከተላቸው ( ከገሊላ) 1፡34-51

- የመጥመቁ ዮሐንስ ደቀመዝሙር ከሆኑት ሁለቱ ዮሐንስ እና እንድርያስ በመጥመቁ ዮሐንስ ምስክርነት ሳቢያ ወደ ኢየሱስ መጡ። ከአስር ሰዓትም በኋላ ***"መሲሁን አግኝተነዋል"*** የሚል ምስከርነት ሰጡ።
- እንድርያስ ደግሞ የስምዖን ወንድም በመሆኑ ወደ (መሲሁ) ይዞት መጣ። ጌታም ባገኘው ጊዜ አንተ ኬፋ (ጴጥሮስ) ትባላለህ አለው ።

- ፊልጶስም በቀጥታ በጌታ የተጠራ ("ተከተለኝ") ሲሆን የሚኖርበትም ከተማ በጴጥሮስ እና በወንድሙ በእንድርያስ ከተማ በቤተ ሰይዳ ነበር።

## ኢየሩሳሌም በኢየሱስ የአገልግሎት ዘመን



- እንድርያስ ደግሞ የስምዖን ወንድም በመሆኑ ወደ (መሲሁ) ይዞት መጣ። ጌታም ባገኘው ጊዜ አንተ ኬፋ (ጴጥሮስ) ትባላለህ አለው ።
- ፊልጶስም በቀጥታ በጌታ የተጠራ ("ተከተለኝ") ሲሆን የሚኖርበትም ከተማ በጴጥሮስ እና በወንድሙ በእንድርያስ ከተማ በቤተ ሰይዳ ነበር።
- ፊልጶስም ደግሞ ናትናኤልን ጋበዘው በሙሴ እና በነቢያት የተመሰከረለትን አግኝተነዋል ብሎ። ናትናኤልም በተነገረው አጭር መገለጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እና የእስራኤል ንጉሥ መሆኑን አምኖ መሰከረ።
    - ❖ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ጉዳዮች - "መጥተህ እይ" "አግኝተነዋል" የሚሉት ቃላት ናቸው። ከክርስቶስ ጋር መዋል የሚያደርገውን እና የሚያስተምረውን ማየት በእርግጥ የእርሱን ማንነት በውል መረዳት ሰጥቶአቸው ሥለ ነበር የምንጠብቀው አሊያም የምንፈልገውን አግኝተነዋል የሚል የልብ ድፍረትን ሰጥቶአቸዋል።

4.3. በገሊላው ቃና መንደር የተደረገው የመጀሪያው ምልክት 2፡1-11

- ጌታ እንደ ማንኛውም አይሁድ በሠርግ ላይ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ታድሞአል ፤ በሰርጉም መሐል የተፈጠረውን እጥረት በጥራት ላይ ያለውን ጌትነቱን በመግለት ደቀመዛሙርቱ በእርሱ እንዲያምኑ ትልቅ ምልክትን ሰጥቶአል።

4.4. በኢየሩሳሌም በፋሲካ በዓል ላይ ተገኝቶ ያደረገው ምልክት 2፡13-24

- ጌታ እንደ ማንኛውም አይሁድ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለፋሲካ በዓል መጣ በቤተ መቅደስም የሚሆነውን የግብይት ሥርዓት እና የገንዘብ ልውውጫ ተመልክቶ
- "የአባቴ ቤት ቅናት ይበላኝ" ፣ "የአባቴ ቤት የጸሎት ቤት ይባላል እናንተ ግን የንግድ ቤት አደረጋችሁት" ብሎ ጅራፍ ገምዶ እየገረፈ አባረራቸው።
- ይህን በማድረጉ የተወሰኑት አይሁድ ስላለው ስልጣን ምልክት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ብዙ ሰዎች ግን በእርሱ መሲሕነት አምነዋል።
- ደቀመዛሙርቱ ግን ከሞቱ እና ከትንሣኤው በኋላ መፃሕፍት የሚሉትንና እርሱ የተናገረውን ነገር እውነት መሆኑ ስለ ገጠመላቸው " ይህንን ቤት አፍርሱት በሶስተኛውም ቀን አስነሳዋሁ" ማለቱን አመኑ።

4.5. መሲሁ ከአይሁድ የምኩራብ አለቃ ከፈሪሳዊው ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ውይይት 2፡25-3፡21

- ኒቆዲሞስ በሌሊት የመጣበት ምክንያት ከአይሁድ ፈሪሳዊያን ለመሸሽግ ሳይሆን አልቀረም፤ የውይይቱም ስፍራ በሐዋርያው (በጌታ ደቀመዝሙር) በዮሐንስ የመኖሪያ ቤት ሳይሆን አይቀርም።
- የውይይቱም ዋና አጀንዳ

- "ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ዳግመኛ መለወለድ አለበት ይህም ከውሃ እና ከመንፈስ"።
- "ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል"
- የሰዎች ልጆች ብርሃንን የሚጠሉበት ዋና ምክንያት ሥራቸው ክፉ በመሆኑ ነው፤
- ስለዚህም ወደ ብርሃን መምጣት አይወዱም፣ሥራቸው በብርሃን ስለሚገለጥ፤

4.6. "መሲሁ" ለሳምራዊቷ ሴት መገለጡ/ መታወቁ ( ጉዞ ወደ ገሊላ በሰማሪያ በኩል) 4፡1-41

- ብዙ ደቀመዛሙርትን እያጠመቀ እና እያበዛ እንዳለ አይሁድ መስማታቸውን ጌታ ባወቀ ጊዜ ይሁዳን ለቅቆ ወደ ገሊላ መሔድን ፈለገ፤ መሆኑም በሰማርያ በኩል ለማለፍ ግድ ሆነበት፤
- ውሃ ልትቀዳ ከሰማርያ ከተማ ከወጣች ከአንዲት ሴት ጋር ሲካር በምትባል ያዕቆብ ውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተገናኙ አነስተኛ በሚባል መገለጥ መሲህነቱን ተገነዘበች፤ ወደ ከተማ ሔዳ ለሕዝቦቿ ተናገረች
- ደቀመዛሙርቱም ምግብ አመጡ ነገር በዚህ ምግብ ሳቢያ መሲሁ ትምህርትን አስተማረ
  - "የእኔስ መብል የላከኝ ፈቃድ መፈጸም ነው ...."
  - አዝመራው እንደ መጣ ተመለከቱ የሚዘራ እና የሚያጭድ ዋጋቸው እኩል ነው...
- የከተማውም ነዋሪዎች መጡ አብሮአቸው እንዲቆይ ጠየቁተ ነገር ግን ሁለት ቀን በእነርሱ ዘንድ አሳለፈ በእርግጥ ወደ ዓለም የሚመጣው የዓለም መድኃኒት መሆኑን አመኑ፤

4.6. መሲሁ በገሊላ ተቀባይነት ማግኘቱ 4፡43-45

- በኢየሩሳሌም በፋሲካ በዓል መጥተው የነበሩ ያደረገውን ምልክት አይተው ስለ ነበር ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤
- ከቅፍርናም የሆነ ሰው ኢየሱስ ወደ ገሊላዋ ቃና እንደመጣ ሰምቶ በሞት አፋፍ ላይ ያለውን ልጁን እንዲፈውስለት ለመነው፤ መሲሁም ልጅህ በሕይወት አለች ሒድ አለው፤ በዚያችም ሰዓት ብላቴናው ተፈወሰ በዚህም ሳቢያ እርሱ እና ቤተሰቦቹ በመሲሁ አመኑ።

**<u>ማጠቃለያ</u> ፡-** ሰዎች ጌታን እንዴት በቀላሉ እንደተቀበሉት በሚከተሉት መንገዶች ማየት ይቻላል።

✓ በሰው ምስክርነት የዳኑ

- ዮሐንስ - በመጥመቁ ዮሐንስ ምስክርነት አመኑ!
- እንድርያስ - በመጥመቁ ዮሐንስ ምስክርነት አመኑ!
- ጴጥሮስ በወንድሙ - በእንድርያስ ምስክርነት አመነ!
- ፊልጶስ - በናትናኤል ምስክርነት ዳነ!
- የሰማርያ ከተማ - አምስት ባሎች በነበሯት ሴት ምክርነት ጌታን አገኙ!

- ✓ በታምራት ያመኑ
    - 12 ደቀመዛሙርት - ውሃ ወደ ወይነጠጅ በመለወጡ አመኑ
    - የኢየሩሳሌም ሰዎች እና የገሊላ ሰዎች በፋሲካ በዓል ላይ ጌታ ባሳየው ቅናት ምክንያት አመኑ!
    - የሹም ቤተሰብ በተደረገላቸው የፈውስ ኃይል ምክንያት ቤተሰቡ በሙሉ ዳነ!
- ✓ ጌታ ራሱ የተገናኛቸው
    - ናትናኤል በራሱ በጌታ ጥሪ ተርሳለት ዳነ!
    - ሳምራዊቷ ሴት - ጌታ ራሱ ተገናኛት!
- ✓ በራሳቸው ወደ ጌታ የመጡ እና የዳኑ
    - ኒቆዲሞስ - በራሱ መጥቶ ጌታን አግኝቶ አመነ!

# 5. የመሲሁን አገልግሎት አይሁዶች በጥርጣሬ በማየታቸው ምክንያት አለመግባባት መብቀል የጀመረበት ጊዜ 5፡1-6፡71

- መሢሁ በአይሁድ መካከል በነበረው አገልግሎት አለመግባባት የተፈጠረበት ወይም የተወለደበት ጊዜ በተለይም በዮሐንስ ዘገባ መሰረት በሁለት ተዓምራቱ ላይ ተመስርቶ ነበር የተፈጠረው።

5.1. ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመውን ሰው መፈወሱ 5


1-15 - የታዓምራቱ ሂደት

- መሲሁ ለአይሁድ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር። በእርግጥ ይህ በዓል የትኛው እንደ ነበር በውል አልተገለጠም።
- ቤተ ሰይዳ በምትባል በበጎች በር አጠገብ አምስት መግቢያ እና መውጫ በር ያላት የውሃ መጥመቂያ ቦታ ላይ ለ38 ዓመት ለፈውስ የተኛ ሰው ነበር
- ጌታ ሰውዩም ለዚህን ያህል ዓመት በዚህ ቦታ እንደነበር አውቆ ፈቃደኝነቱ ከጠየቀው በኋላ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ በማለት ብቻ ፈወሰው። ይህም ፈውስ የተከናወነበት ዕለት ቅዳሜ ነበር ማለትም የአይሁድ ሰንበት ነበር።

15-47 - ላለመግባባት እንደ መንስዔ የሚታዩ ሐሳቦች በትምህርት መልክ የተገለጠበት ክፍል

- ከአይሁድ ጋር ያለመግባብት መንስዔ የሆነው በሰንበት ቀን መፈወሱ እና የፈወሰውን ሰው በሰንበት ቀን አልጋውን ተሸክሞ እንዲሄድ ማዘዙ ነበር።

- ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ እራሱን ከአባቱ ጋር እኩል ማድረጉ ነበር (አብ እና ወልድ እኩል ስለመሆናቸው ማስተማሩ) እኩል ያደረገባቸውም ነጥቦች፤
    - አባተ እስከ ዛሬ ድረስ ይሰራል እኔም እሰራለሁ በማለቱ ፤
    - አባቱ የሚያደርገውን እና የሚያሳየው እንጂ ከራሱ ምንም እንደ ማያደርግ፤
    - አባቱ ሕይውት እንደሚሰጥ ልጁም ሕይወት ይሰጣል ማለቱ፤ በመሆኑም ሙታን ሁሉ ድምጹን የሚሰሙት ሰዓት አሁን መሆኑን መናገሩ፤ የሚሰሙትም በሕይወት እንደሚኖሩ መነጋሩ፣
    - አባቱ እንደ ሚከበር ሁሉ ልጅም እንዲከበር ፍርድን መፍረድ ለልጁ መሰጠቱ ከመቃብር ያሉት ሁሉ የቅንነቱን ፍርድ ከእርሱ እንደሚቀበሉ መናገሩ፤
    - ሕይወትን የሚሰጠው አባቱ እንደ ነበር ሁሉ ከዚህ በኋላ ሕይወት የሚሰጥ ልጁ እንዲሆን መደረጉ፤
- ይህን ሁሉ መናገሩ በእርግጥ እውነት ነው እራሱ ራሱ ስለ ራሱ መመስከሩ እውነት ሊያስብለው ባይችልም
    - መጥመቁ ዮሐንስ መስክሮአል
    - ሙሴ መስክሮአል
    - መጻሕፍት ስለ እርሱ መስክረዋል
    - አብ የሰጠው ሥራ እርሱ ይመስክራሉ።


Traditional site of Sermon on the Mount
Jesus performs numerous miracles
Jesus calls Levi, Simon, Andrew, John, and James
Jesus teaches and heals
N
Chorazin
GAULANTIS
Bethsaida
Feeding of the multitudes
Plain of Gennesaret
Plain of Bethsaida
Heptapegon (Tabgha)
Gennesaret
Jesus appears to His disciples on the Sea
Arbela
Taricheae (Magdala)
Sea of Galilee
Gergesa
W
E
Jesus heals a demoniac
Tiberias
LOWER GALILEE
Hammath
Hippos
Jesus calms a storm
Home of Mary Magdalene
Sennabris
Emmatha
Jordan R.
Yarmuk R.
Gadara
DECAPOLIS
S
108
THE MINISTRY OF JESUS AROUND THE SEA OF GALILEE
MATT. 5–7; 9:1–9
MARK 1:21–34; 2:1–14; 4:–41; 5:1–20; 6:45–52
LUKE 7:1–10; 9:12–17
JOHN 6:1–25
City
Road

5.2. መሢሁ አምስት ሺህ ሕዝብ በታዓምራት መመገቡ 6

1-15 - የታዓምራቱ ሂደት

- የአይሁድ የፋሲካ በዓል ቀርቦ ነበረበት ወቅት ነበር፤
- መሲሁ በገሊላ ባህር ማዶ ወይም በጥብርያዶስ ተሻግሮ ነበር፤
- በመሲሁ የተደረጉትን ምልክቶች ስላዩ ብዙ ሰዎች ተከተሉት፤
- ለተከተሉት ለእነዚህ ሕዝብ በሁለት ዓሳ እና በአምስት እንጀራ ከ20 ዓመት በታች ወንዶች እና ሴቶች ሳይቆጠሩ አምስት ሺህ ሕዝብ መገበ፤
- ከእነርሱም ተበልቶ 12 መሰብ ምግብ ተረፈ።
- ይህንንም ምልክት ሕዝቡ ባየ ጊዜ ወደ ዓለም የሚመጣው ነብይ ነው ብለው አሉ፤ ከዚህም የተነሳ ሊያነግሡት እና ከሮም አገዛዝ ነጻ መሆንን አሰቡ።

16-21 - ደቀመዛሙርቱ ወደ ሰፈራቸው ወደ ቅፍርናሆም በጀልባ ላይ ሆነው በመመለስ ላይ ሳሉ ከፍተኛ ነፈስ ተነሳ ባህሩም ተናወጠ፤ መሲሁ በእኩለሌሊት ወደ ደቀመዛሙርቱ በውሃ ላይ እየተራመደ መምጣቱ ለደቀመዛሙርቱ የፍርሃት ምክንያት ቢሆነም ነገር ግን "እኔ ነኝ" አትፍሩ በማለት በሰላም ወደ ምድር ደረሱ።

22-71 - በበነጋውም ሕዝቡ ታዓምራት በተደረገበት ስፍራ መሲሁን ሊፈልጉ መጡ ሆኖም ግን እርሱም ሆነ ደቀመዛሙርቱ በዚያ ስፍራ አልነበሩም በመሆኑም እየፈለጉአቸው ወደ ቅፍርናሆም መጡ። ባገኙቱም ጊዜ መቼ ወደዚህ ስፍራ እንደመጣ ጠየቁት በዚህ ጥያቄ እና መልስ ሳቢያ ያለመግባባቱ መንስዔ የሚሆኑ ትምህርቶች ተፈጠሩ፤

- ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ሥሩ (ይህም በላከው በልጁ ማመን ነው።)
- ከሰማይ እንጀራን የሰጣችሁ አባቴ ነው፤ የእግዚአብሔር እንጀራ ሕይወትን የሚሰጥ ነው
- ከሰማይ የወረደ *የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤* ወደ እኔ የሚመጣም አይራብም አይጠማም ፣ ከቶ ወደ ውጭም አይጣልም። (እናውቀየም የለም እንዴ እንዴት ከሰማይ ወርድሁ ይላል አሉ)
- እኔም ለዓም የሚሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው። ሥጋዬ እውነተኛ መብል፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው አላቸው። ስጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠታ የዘላለም ሕይወት አለው አለ። ብዙዎቹም አንጎራጎሩ።
- ይህ ንግግሩ እንዳሰናከላቸው አውቆ እንግዲህ የሰው ልጅ ወደ ነበረበት ክብሩ ሲመለስ ብታዩ ደግሞ ምን ትሆናላችሁ አላቸው። በዙዎችም በንግግሩ ተሰናክለው ወደ ኋላ ተመለሱ።
- 12ቱን ደቀመዛሙርትም ጠየቀ እናንተስ መሔድ ትፈልጋላችሁን አላቸው? ስምዖን ጴጥሮስም ትክክለኛ እምነታቸውን ገለጠ።

  **<u>ማጠቃለያ</u>** ፡- በአይሁድ ማህብረሰብ መካከል በመሲህነቱ ያለማመንና መግባባት ያለመቻል የተወለዱበት ምክንያቶች በእውነቱ እነዚህ ነጥቦች ለአንድ አይሁድ እጅግ ጸያፍ የሆኑ ነገሮች ናቸው።

- ✓ ሰንበትን ስለ ሻረ (በሰንበት ቀን መፈወሱና አልጋ እንዲሸገም ማዘዙ ማለትም ስራ ማሰራቱ)፤
- ✓ እራሱን ከአባቱ ጋር እኩል ማድረጉ፤ (ለአይሁድ እራሱን አምላክ ማድረግ)
- ✓ ከሰማይ ወርጃለሁ ማለቱ፤ (ለአይሁድ እግዚአብሔሔርን መሳደብ ነው)
- ✓ ስጋዬን ብሉ ደሜንም ጠጡ ማለቱ (ለአይሁድ ሰው መብላት ጸያፍ ነው)

# 6. በመሲሁ አገልግሎት አይሁዶች ባለማመናቸው ምክንያት የክርክር እና የጭቅጭቅ ጊዜ 7፡1-10፡39

- በዚህ በዮሐንስ ዘገባ ውስጥ አይሁድ በኢየሱስ መሲህነት ላይ ጉልይ የሆነ ክርክር እና አለመግባባት በመካከላቸው እንኳ ሳይቀር የተፈጠረበትን ወቅትን ነው የሚያሳየን። በዳስ በዓል ላይ ፣ በአመንዝራነት በተያዘችውን ሴት ምክንያት እና ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረውን ሰው በመፈወሱ ሳቢያ የተከሰቱ ጭቅጭቅና ንትርኮች ናቸው።

6.1. መሢሁ በአይሁድ ዳስ በዓል 7፡1-52

- አስቀድሞ በተፈጠሩት ያለመግባባት ምክንያቶች ኢየሱስን የመገደል ፍላጎት በአይሁዶች ዘንድ ተፈጥሮአል፤ በእነርሱ እይታ ልክ ነበር ፤ ምክንያቱም ያለመግባባት መንስዔ ተብለው የተገለጡት ሐሳቦች ለአይሁድ ማህበረሰብ በድንጋይ ተወግሮ የሚያስገድል በመሆኑ ነው። ሰንበትን መሻር፣ እራስን አምላክ ማድረግ፣ እራስን ከአብ እኩል ማድረግ እንዲሁም ከሰማይ ወርጅላሁ ማለት የሞት ፍርድ የሚያሰጡ ናቸው።
- በዚህም ሳቢያ ኢየሱስ በይሁዳ ማገልገሉን ለጊዜው አቁሞ በገሊላ ነበር የሚያገለግለው ፤ ይህም ነው የገሊላው ታዓምራቶቹ ከኢየሩሳሌም ከተደረጉት በቁጥር የሚበዙት፤
- የአይሁድ ዳስ በዓል ቀርቦ ሳለ ወደ በዓሉ ወደ ይሁዳ እንዲሄድ እና እራሱን ለዓለም እንዲገልጥ የሥጋ ወንድሞቹ የለበጣ ንግግር ይናገሩት ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ወንድሞቹ ገና በውድማቸው መሲህነት አላመኑም ነበር።
- በበዓሉ ላይ የነበሩት አይሁዶች ስለ መሲሁ ያላቸው እይታ በሶስት የተከፈሉ ይመስላሉ
    1. ደግ ሰው ነው
    2. ደግ ሰው አይደለም ክፉ ነው
    3. ሕዝብን ግን ያሳስታል (አሳሳች ነው)
- በራሱ ሰዓት እና ጊዜ ወደ በዓሉ ተሰውሮ ወጥቶ በመቅድስ ሲያስተምር በልባቸውም ሆነ በአፋቸው ለሚናገሩት ሃሳብ እና ጥያቄ ቀጥታ መልስ መሲሁ በበዓሉ ላይ ከሰጣቸው ትምህርቶች ጭቅጭቅቶች ማደግ ጀመሩ፤
    1. ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ሊያውቅ ቻለ? የመሲሁ መልስ - የእኔስ ትምህርት ከላይ ከአባቴ ነው ከራሴ አይደለም

2. ስለምን ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ ? የሕዝቡ መልስ ጋኔን አለብህ ማን ሊገድልህ ይፈልጋል፤
3. ስለምን በቅን/በትክክል አትፈርዱም? በሰንበት ቀን ሙሴ ነው ያዘዘን ብላችሁ ሰው ትገርዛላችሁ ታዲያ በሰንበት ቀን እኔ የታመመን ሰው ሙሉ ጤና ሳደርገው እንዴት ሰንበትን መሻር ይሆናል?
4. መሲሁ ሲመጣ ከወዴት እንደሚመጣ አይታወቅም ነገር ግን ይህ ከወዴት እንደመጣ እናውቃለን የሕዝቡ አስተያየት። ከወዴት እንደ መጣሁ ታውቃላችሁ ነገር ግን የላከኝ እርሱ እውነተኛ ነው።
5. ከሕዝቡ መሲሁስ ቢመጣ ከዚህ ሰው የተሻለ ምልክቶችን ሊያሳይ ይችላል ?
6. የካህናት አለቆች እና ፈሪሳዊያን ሕዝቡ እንዳንጎራጎሩ (የሕዝቡ መሪዎች የዚህን ሰው ማንነት አውቀው እና አጣርተው ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ነበረባቸው የሚል ስሜት በሰው ሁሉ ውስጥ መፈጠሩን) አውቀው እንዲያዝ ሎሌዎችን ላኩ ፤
7. በዙዎች በትምህርቱ ይህ ሰው መሲሁ ነው አሉ ነገር ግን የተወለደበትን ቦታ አለማወቃቸው (ማለትም በዳዊት ከተማ በቤልሔም መወለዱን) ደግሞ መስናክል ሆነባቸው ፣ እርስ በእርሳቸውም መለያየት ሆነባቸው። ሎሌዎቹም በመሲሁ ንግግር አለም ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲህ የሚናገር ሰው የለም ብለው ተገርመው ተመለሱ፤
8. ፈሪሳዊያኑ ሕዝቡን መርገማቸው መሲሁንም አሳች ማለታቸውን ኒቆዲሞስ ከሕግ አንጻር ለማሳየት ሞከረ ነገር መግባባት አልቻሉም። በመሆኑም ሁሉም ወደየቤታቸው ሄዴ ብሎ ዘጋቢው እንዴት እንደተበታተኑ የሳየናል።

6.2 መሲሁ እና አመንዝራይቱ ሴት 7፡53-8፡59

- መሲሁ ግን ወደ ደብረዘይት እንደ ተለመደው ህይወቱ ለጸሎት ሔደ።
- በማግስቱም በማለዳ ወደ ቤተ መቅደስ ደረሰ ሕዝብን ማስተማር ጀመረ።
- ጸሐፍትና ፈሪሳዊያን ግን በምንዝር የተያዘች ሴት ይዘው ወደ እርሷ መጡ ምክንያታቸው ደግሞ የሚከሱበትን እና የሚፈትኑበትን ለማግኘት ነው።
- የሙሴ ሕግን ሲቃወም በትክክል አግኝተዋነዋል ለማለት ነበር፤ ይሁን እንጂ እርሱ ግን በማንም ላይ አልፈርድም ብሎ ሁሉም ኃጢያተኛ መሆናቸውን ሊያሳያቸው ቻለ። በስተመጨረሻም ከሳሾቿም ቢሆን እንኳ ሊፈርዱባት አልቻሉም እነርሱም ኃጢየተኞች ነበሩና።
- ይህንን ክስተት ተከትለ የመጣው አለመግባት ወደ ጭቅጭቅ አደገ ፤ ይህም ደግሞ በትምህርት ውስጥ የተገለጠ ነው፤

   1. መሲሁ ስለ መፈረድ የሰጠው ትምህርት

- ኢየሱስም፦ እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት። እኔ በማንም አልፈርድም ፣ ነገር ግን እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም።የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው አላቸው።
- *እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤* የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው ለከሳሾቹ።

2. የእነርሱ - መልስ አንተ ስለ ራስህ ትመስክራለህ? የመሲሁ መልስ የላከኝ አባቴ ስለ እኔ ይመስክርልኛል ምስክርነቴም እውነት ነው።
3. አንተ ማነህ? እኔ አስቀድሞ ስለ ራሴ ተናግሬአለሁ  ነገር ግን እናንተ እኔ መሲሁ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢያታችሁ ትሞታላችሁ።በዚህ ትምህርቱም ብዙዎች መሲሁ መሆኑን አመኑ። ያመኑትንም በዚህ እውነት ብትኖሩ አርነት ትወጣላችሁ ምክንያቱም እውነት አርነት ያወጣችኋል አላቸው።
4. አይሁድ ስለ ራሳቸው ያለቸው እይታ ከሐሰቡ ጋር ሊያግባባቸው አልቻለም
   - እኛ የማንም ባሮች አይደለንም ምክንያቱም የአብርሃም ልጆች ነን፤ አርነት ትወጣላችሁ አትበለን፤
   - የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ አብርሃም የሚያደርገውን ታደርጉ ነበር፤ ነገር ግን የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ ምክንያቱም ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ!
5. እነርሱም መልሰው ሳማርዊ መሆንህ ጋኔንም አለብህ ማለታችን ልክ ነን፤
6. አንተ ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣህ የአይሁድ ጥያቄ ነበር? የእርሱ መልስ ግን አብርሃም ቀኔ ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ ለአቸው ይህም አልገባቸው ሲል አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርሁ ሲል ሊወግሩት ድንጋይን አነሱ።

6.3 ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረው ሰው መፈወሱ 9፡1-41

1-7 የፈውሱ ሂደት

- የእግዚአብሔር ሥራ እንዲገለጥ ምክንያት የሆነው ይህ ሰው ጌታ ዓይኑን በጭቃ ቀብቶ ሄዶ በሰሊሆም መጠመቂያ ውሃ እንዲታጠብ አዘዘው
- በሰሊሆን የመጠመቂያ ውሃ ታጥቦ ሲመለስም እያየ መጣ፤ ይህም ፈውስ የተደረገበት ቀን ዕለተ ቅዳሜ ሰንበት ነበር።

7- 34 በተፈወሰው ሰው ምክንያት የመጣ ክርክር

- በዚህም ፈውስ ምክንያት በፈሪሳዊያኑ መካከል መለያየት ሆነ ምክንያቱም ይህ ሰው ሰንበትን ስለ ማያከብር ከእግዚአብሔር አይደለም ኃጢያተኛም ነው፣ ሌላው ደግሞ ፈጽሞ እንደነዚህ ዓይነቱን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል ሰው ኃጢያተኛ ሊሆን አይችልም።
- በተፈወሰው ሰው እና በፊሪሳዊያኑ መካከል በመሲሁ ላይ ክርክር ሆነ ባለመግባባት እና በጭቅጭቅ ተለያዩ ወደ ውጭም አወጡት

35-10፡22 በተፈጠረው ችግር ምክንያት መሲሁ የሰጠው ትምህርት

- የተፈወሰው ሰው ወደ ውጪ እንዳወጡት ሰማ ስለዚህም ሊያገኘው ወደደ ባገኘውም ጊዜ በመሲህነቱ እንደሚያምን ጠየቀው አዎ አምናለሁ ብሎ መለሰለት ወድቆም ሰገደለት። ኢየሱስም፡- የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ አለ። ይህም ንግግር ፈሪሳዊያንን አስከፋቸው፤ የክርክሩ መነሻም ሆነ
- በምሳሌም ተናገራቸው
  - እውተኛው *የበጎች በር እኔ ነኝ* እረኛው በበር ይገባል በጎቹም ድምጹን ይሰሙታል ፤ ሌባው ግን በሌላ መንገድ ይገባል፤
  - *መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣* በጎቼ ያውቁኛል እኔም አውቃቸዋለሁ ነፍሴንም ስለ እነርሱ አኖራለሁ ፤
  - ከዚህ በረት ያልሆኑ በጎች አሉኝ እነርሱንም ላመጣ ይገባኛል ፤ ድምጼን ያውቃሉ ይሰማሉም፤
  - በዚህ ሐሳቡ እንደገና በአይሁድ መካከል መለያየት ሆነ ግማሹ ጋኔን አለበት ስለምን ትሰሙታላችሁ ይላል፣ሌላው ደግሞ ጋኔን ያለበው ሰው እንዲህ ዓይነት ንግግር ሊናገር አይችልም ደግሞም እውር አያበራም።

10፡22-39 - በኢየሩሳሌም የመቅደስ መታደስ በዓል ላይ

- በክረምት ወራት ለበዓል በኢየሩሳሌም ተገኝቶ ሳለ እስከ መቼ በጥርጣሬ ታቆየናለህ ላሉት ጥያቄ የሰጠው መልስ እናንተ የማትሰሙኝ ዋናው ምክንያት በጎቼ ስላልሆናችሁ ነው ብሎ መለሰላቸው።
- በጎቼን እኔ አውቃቸዋለሁ እነርሱም ያውቁኛል ድምጼንም ይሰማሉ ይከተሉኛል ደግምም አባቴ ስለ ሰጠኝ ማንም ከእጄ አይነጥቃቸውም ሲላቸው ሊወጉሩት ድንጋይ አነሡ።
- እራስህ ሰው ስትሆን አምላክ በማድረግህ ነው የምንወግርህ አሉት። ሊይዝቱም ፈለጉ ነገር ግን ጊዜው አልነበረም።

# 7. የመሲሁ አገልገሎት በአይሁዶች መካከል የፈጠርው ጭቅጭቅ ወደ ግድያ መፈለግ ያደገበት ጊዜ 10:40 - 12፡36

ዘጋቢው በዚህ ክፍል ሊያስጨብጠን የሚሞክረው የመሲሁን አገልግሎት ይልቁንም የሚያደርገውን ተዓምራት እና ትምህርት ካለመግባባት ወደ ጭቅጭቅ እና ንትርክ አድጎ እርሱን ወደ መግደል ደረሰ።

7.1 የአልዓዛር ከሞት መነሳት

የታዓምራቱ ሂደት 10፡40-11፡ 53

- መጥመቁ ዮሐንስ ያጠምቅበት ወደ ነበረበት ከዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ በቤተ ራባ መንደር መጣ። በዚያም መሲሁ ከዮሐንስ ይልቅ የበለጠ ምልክት በማድረጉ በመሲሁ ብዙዎች አመኑ።
- ከይሁዳ ቢታንያ ከሚወዳቸው ቤተሰቦች ከማርታ እና ከማርያም ዘንድ ወንድማቸው መታመሙን ላኩበት ፤ ይህም ሕመም ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ሕመም እንደሚሆን እንጂ ለክፉ እንደማይሆን አውቆ ከመሔድ አራት ቀን ቆየ።
- እነርሱ እንዳሰቡት መሲሁ በጊዜ አልደረሰም አልዓዛርም ሕመሙ በረታበት ሞተ። እንደ አይሁድ ልማድም ተቀበረ!
- በአራተኛው ቀን መሲሁ መጣ ሁሉም ነገር እንዳከተመ አሰቡ፤ እርሱ ግን *ትንሣኤ እና ሕይወት እኔ ነኝ* ማንም በእኔ መሲህነት ቢያምን ከሞት ወደ ሕይወት ይሻገራል እንጂ አይሞትም አለ።
- አልዓዝርንም ከመቃበር በሕይወት እንዳለ ተገንዞ ወጣ። አብረውም ከነበሩት አይሁዶች መካከል ብዙዎች በመሲህነቱ አመኑ። የተቀሩት ግን ለፈሪሳዊያን የሆነው ነገር ሁሉ ነገሩ። ይህም የመሲሁ የታዓምራት አገልግሎት በአይሁድ መካከል የመጨረሻው እንዲሆን አደረገው።

መሲሁ በኤፍሬም ምድረበዳ 11፡54-57

- ብዙዎችን ከማሳቱ በፊት እርሱ አስቀድሞ እንዲገደል ተማሙ በመሆኑም ያለበትን ቦታ የሚያውቅ ሁሉ ጥቆማ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ሰጡ። መሲሁም አገልግሎቱ ውደ ፍጻሜ በመድረሱ እንቅስቃሴውንም ከይሁዳ እና ከገሊላ ወደ ኤፍሬም ምትባል መንደር በምድረበዳው በኩል ከደቀመዛሙርቱ ጋር እስከ ፋሲካ በዓል ድረስ በዚያ ተቀመጠ።

ከፋሲካ ከ6 ቀን በፊት ከኤፍሬም ምድረ በዳ በይሁዳ ቢታንያ ወደ ወዳጆቹ ቤት መጣ 12፡1-11

- በማርያም ማርታ እና አልዓዛር ቤት የእራት ግብዣ ተደረገለት፤ ማርታ ታገለግል ነበር፤ ማርያምም ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ሽቱ ገዝታ እግሩን ትቀባ ነበር በጸጉሯም ታብሰው ነበር።

- የአስቆርቱ ይሁዳ ግን ስለምን ይህንን ሽቶ ታባክናለች ተሸጦ ለድሆች ቢታደል አይሻልም የሚል ሀሳብ አቀረበ ፣ ይሁን እንጂ ለድሆች አዝኖ ሳይሆን እርሱ ገንዘብ ያዥ ስለሆነ ከብሩ ለመጠቀም ፈልጎ እንደነበር ጸሐፊው ይነግረናል።
- አልዓዛርም በዚያ ተቀመጦ ነበር ብዙ አይሁዳዊያን እርሱን በማየት ብቻ በመሲሁ ያምኑ ነበር። በመሆኑም የካህናት አለቆች አልዓዛርም መገደል እንዳለበት አቀዱ።

መሲሁ በግልጥ እንደ አይሁድ ንጉስ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ 12፡12-26

- የከተማይቱ ሕዝብ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ተቀበሉት
- አልዓዛርን ሲያስነሳ ከእርሱ ጋር አብረው የነበሩ ሁሉ ይመሰክሩለት ነበር
- ፈሪሳዊያንም ምንም ማድረግ እንዳልቻሉ ተረደተዋለ።
- በዚህ መሐልም ከግሪክ አገር የመጡም ጌታን ማየት ፈልገው ነበር ይሁን እንጂ ለተላኩት የጊዜውን ሐሳብ መሲሁ ተናገረ
    - የሚከብርበተ ሰዓት እንደ ደረሰ
    - ካልሞተ ብዙ ፍሬ ማፍራት እንደማይችል
    - እርሱን ማገልገል የሚፈልግ ካለ መንገዱ እርሱን መከተል ብቻ እንደሆነ ተናገራቸው።

# 7. መሢሁ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብቻ ያደረገው ልዩ የስብሰባ ጊዜ እና ጸሎቱ 13፡1-17፡26

ዮሐንስ በዚህ ክፍሉ ውስጥ መሲሁ በምድር አገልግሎቱ መጨረሻ ላይ በኢየሩሳሌም ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብቻ ያደረገውን የውይይት፣ የምክር፣ የማጠቃላያ ሐሳብ ጸሎት የጸለየበት ክፍል ነው።

7.1 የፋሲካ እራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር 13፡1-38

- ለደቀመዛሙርቱ ያለውን የመጨረሻ ፍቅር የገለጠበት እንዲሁም ታላቅ የሆነውን ትሕትና እግር በማጣብ ያሳያቸው ጊዜ ነው። 1-20
- በዚህም መሐል በመንፈሱ ታወከ ከእናንተ መሐል አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። በደቀመዛሙርቱም መካከል የመያያ አጀንዳ ሆነ። 21-30
- እርሱ ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ጋር ሰለማይኖር እርሱ በእርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ መከራቸው ፤ የእርሱ ደቀመዛሙርት መሆናቸው የሚታወቀው በፍቅር በመመላለሳቸው እንደሆነም ጭምር አሳሰባቸው ፤ 31-35
- ጴጥሮስ መሲሁ ስለ መካዱ አስቀድሞ የተሰጠ ትንቢት 36-38

7.2 ጌታ የደቀመዛሙርቱን ልበ ያበረታታበት ቃል 14፡1-50

- እሔዳለሁ ደግሞም ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ነገር ግን ጥቂት ጊዜ ደግሞ አታዩኝም ማለቱ የደቀመዛሙርቱን ልብ አውኮ ነበር፡፡
- በመሆኑም ወደ አባቱ እንደሚሔድ በዚያም መኖሪያን እንደሚያዘጋጅላቸው በመናገር አጽናናቸው፡፡
- ትዕዛዙን እንዲጠብቁ ይኸውም እርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ ሲሆን ሌላ አጽናኝም እንደሚልካላቸው ተስፋ ገባላቸው፡፡

7.3 ስለ መንፈሳዊ ሕብረት አስፈላጊነት 15፡1-27

- ደቀመዛሙርቱ ከጌታቸው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ መንፈሳዊ ሕብረት 1-11
- ደዘመዛሙርት እርስ በእርስ ሊኖራቸው ስለሚጋባ መንፈሳዊ ሕብረት 12-17
- አማኞች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ሊኖራቸው ስለሚገባ መንፈሳዊ እይታ 18-27

7.4. ጌታ የጸለየው የመጨሻ ጸሎት 17

- አባቱ የሰጠውን ሥራ ፈጽሞ እንዳከበረው አስቀድሞ በነበረው ክብር እንዲያከብረው 1-5
- ከአብ የተቀበላቸውን በዓለም ሳሉ እንዲጠብቃቸው መጸለዩ 6-19
- ስለ ደቀመዛሙርቱ አንድነት መጸለዩ 20-26

# 8. የመሲሁ መገደል እና ትንሳዔው 18፡1-20፡31

በዮሐንስ የታሪክ ዘገባ ውስጥ ይህ ክፍል የወንጌል እምብረት ነው፡፡ ምክንያቱም የመሲሁ መገደል ከሞት መነሳት እና ማረግ ላይ ነው ክርስቲያና መሰረቱን የጣለው፡፡ በመሆኑም ታሪካዊ እውነታውን በማጤን በውስጡ ያለውን ሥነ-መኮታዊ ሐቅ ደግሞ ለሕይወታችን የተከፈለ ታላቅ ሥራ በመሆኑ ዘወትር ልናስበው ይገባል፡፡

8.1. የመሲሁ መያዝ 18፡1-11

- ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብቻ ከእራት በፊት እና በኋላ ያለውን ጊዜ ከሳለፉ በኋላ ከቄዶሮን ማዶ ባለው የአትክልት ስፍራ እንደ ተለመደው ለጸሎት መጣ፡፡ በእርግጥ ይህንን ስፍራ የአስቆርቱ ይሁዳ ያውቀው ነበርና ማንም ሰው አድራሻውን የሚያውቅ ጥቆማ እንዲሰጥ ባሉት መሰረት የካህናት አለቆች በእርሱ መሪነት ጋሻ እና ጦር ገመድም ይዘው መጡ፡፡
- መሲሁም ተገለጦ እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደኋላቸው ሔደው ወደቁ፣ ጴጥሮስም ሰይፉን አንስቶ የሊቀ ካህኑን ባሪያ ጆሮው ቆረጠ ጌታ ግን ከለከለው የመጣውን ጽዋ ልጠጣ ይገባኛል በማለት፡፡

8.2. መሲሁ በሊቀ ካህኑ በሐና ፊት ቀረበ 18፡12-27

- ሐናም ስለ ትምህርቱ እና ስለ ደቀመዛሙርቱ ጠየቀው ፣ መሲሁም ለጥያቄው መልስ በቀጥታ አልሰጠውም፤
- በመለሰው መልስ የሊቀ ካህኑ ሎሌ መሲሁን በጢፊ መታው

- ጴጥሮስም አስቀድሞ መሲሁ እንደ ተናገረው ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ካደው
- ሐና መሲሁ እንደ ተሰረ ወደ ሊቀ ካህኑ ቀያፈ ሰደደው

8.3. መሲሁ በጲላጦስ ፊት 18:29-19:16

- መሲሁ በምን ጉዳይ እንደ ተከሰሰ አይሁድን ጠየቀ፣ እነርሱም ክፉ አድራጊ ነው ብለው መለሱ፤
- በጲላጦስም ፊት መንግስቱ ከዚህ ከምድር እንዳይደለች መሰከረ፤ ስለ እውነት ሊመሰክር እንደተላከ እውነትንም የሚወድ ሁሉ ድምጹን እንደሚሰሙት መሰከረ፤
- እንደ ልማዱም በበዓል አንድ ሰው ለእስር ይፋታላቸው ነበርና እንዲፈታው ሲጠይቃቸው እርሱን አስወግደው ለእኛ በርባን የሚባለውን ወንበዴ ፍታልን ብለው ጮኹ።
- ጲላጦም መሲሁን ገርፎ ሊለቀው ወደደ ፣ ለገራፊዎች ሰጠው የሮም ወታደሮችም እጅግ ተሳለቁበት፤
- ይሁን እንጂ አይሁድ በዚህ ብቻ ሊደሰቱ አልቻሉም ስቀለው አስወግደው እያሉ ጮኹ ፣ በዚህን ጊዜ ጲላጦስ ደነገጠ ምንም ምክንያት አላገኘሁበትም ቢላቸውም እንኳ እራሱን የእግዚአብሔር ልጅ በማድረጉ ከአምላክ እኩል አስተካክሎአል ስለዚህ በእኛ ሕግ ሊገድል ይገበዋል ብለው ጮኹ።
- ጲላጦስም በፍርድ ወንበር ተቀመጠ ከቄሳር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ስለዚህም ይህን አናውቀውም ስቀለው አሉ።

8.4. የመሲሁ መሰቀል 19:17-37

- መስቀል አሸክመው ወደ ጎልጎታ ወሰዱት፤
- በዚየም ከሁለት ወንበዶችም መሐል ሰቀሉት፤
- ልብሱንም እጣ ተጣጥለው ጭፍሮቹ ተከፋፈሉት፤
- ኢየሱስም እናቱን ማሪያምን ለሚወድደው ደቀመዝሙር ለዮሐንስ አስረከበ፤
- ሆምጣጤ በሰፍነግ ሞልተው አጠጡት
- ሁሉ እንደ ተፈጸመ አውቆ እራሱን አዘንብሎ ነፍሱን ሰጠ።

8.5. የመሲሁ መቀበር 19:38-42

- የአርማትያሱ ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ እንደ አይሁድ ልማድ መሰረት ገነዙት
- ማንም ባልተቀበረበት በአዲስ መቃብር ቀበሩት፤

8.6. ትንሣዔው 20

- በፊተኛው ሳምንት ለመግደላዊት ማርያም ተገለጠ 1-18
- ሁለተኛው መገለጥ በተዘጋ ቤት ውስጥ ተስብስበው ሳሉ 19-23

- ሦስተኛው መገለጥ ከስምንት ቀን በኋላ ቶማስ ባለበት 24-29

8.7. የትንሣዔው ማረጋገጫ እና የመጨረሻው ንግግር 21፡1-23

- በጥብርያዶስ ባህር የተገለጠው መገለጥ
  - ጴጥሮስ ፣ቶማስ ፣ ናትናኤል (የገሊላው ቃና) የዘብድዮች ልጆች እና ሌሎች ሁለት ከደቀመዛሙርት ወደ ዓሳ ማጥመድ ተመለሱ ጌታ ባደረገው ታኣምር እንደገነ ወደ በታቸው መለሳቸው።
- ከምሳ በኋላ ለጴጥሮስ አደራ ሰጠው አገልግሎት የፍቅር ምላሽ